የሰ/መ/ቁ. 57378

ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች ፡-** ወ/ሮ አስቴር አርአያ - ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** ወ/ሮ አምሳለ በላይ - ጠበቃ ሽመልስ ሄይስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው ወ/ሮ አምሳለ በላይ የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም. በተሰጠ ውሣኔ በዶ/ር አለኸኝ መኮንንና በወ/ሮ አስቴር አርአያ ላይ ገንዘብ በማስወሰን የፍርድ ባለመብት የሆንኩበት ይፈፀምልኝ ብለው ባስከፈቱት የአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 92421 የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግንቦት 4 ቀን 2002 ዓ.ም. የፍርድ ባለመብት በሌላ መዝገብ ባለዕዳ ሆነው በመ/ቁ. 63974 በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አፈፃፀሙ እየታየ ስለሆነ በዚህ ችሎት የተሰጠው ፍርድ ተቻችሎ እንዲፈፀም የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻው ከትዕዛዙ ጋር ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለ8ኛ ችሎት ይተላለፍ በሚል የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም በዚሁ ትዕዛዝ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የፍዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 56661 ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም. ይግባኝ የተባለበት ትዕዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በሚል ምክንያት የቀረበ ነው፡፡

አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲፈፀም አፈፃፀም የተጠየቀበት የገንዘብ ፍርድ እና በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አፈፃፀም የተጠየቀበት የገንዘብ ፍርድ ተቻችሎ እንዲፈፀም ለከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረበውና ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይተላለፍ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ሰኔ 17 ቀን 2002 ዓ.ም. በተጻፈ ማመልከቻ ገልፀው አቅርበዋል፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ ተብሎ በመታዘዙ ማመልከቻው ለአሁኗ ተጠሪ ተልኮ ቀረበው መልስ እንዲሰጡበት የተደረገ ሲሆን በተጠሪዋ በኩል በጽሑፍ የቀረበው መልስም ለአመልካች እንዲደርሳቸው ተደርጎ በጽሑፍ የመልስ መልስ ሰጥተውበታል፡፡

በዚህ ጉዳይ በአንድ በኩል የአሁኗ ተጠሪ በአሁኗ አመልካች እና በሌላ አንድ ሰው ላይ ገንዘብ በማስወሰን በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አፈፃፀም የጠየቁበት ፍርድ በሌላም በኩል የአሁኗ አመልካች በአሁኗ ተጠሪ ላይ ብቻ ገንዘብ በማስወሰን በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አፈፃፀም የጠየቁበት ፍርድ መቻቻል ሊደረግበት እንዲችል ለከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረበው የአፈፃፀም ጥያቄ ወደ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተላልፎ ይታይ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት መኖር አለመኖሩ ሲመረመር፡-

በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 397/1/ ላይ እንደተመለከተው በዚህ ጉዳይ ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች በየበኩላቸው ክስ አቅርበው አንዱ በአንዱ ላይ የፍርድ ባለገንዘብ መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን ሁለቱም እንደፍርዱ እንዲፈፀምላቸው ለፍ/ቤት የአፈፃፀም ማመልከቻና ለማቅረብ የአፈፃፀም መዝገብ አስከፍተዋል፡፡ ልዩነት የታየው የአሁኗ አመልካች የአፈፃፀም ማመልከቻውን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበው የአፈፃፀም መዝገብ ማስከፈታቸው እና የአሁኗ ተጠሪ ደግሞ የአፈፃፀም ማመልከቻውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረብ የአፈፃፀም መዝገብ ያስከፈቱ ሆኖ መገኘታቸው ላይ ቢሆንም ፍርዱ በአንድ ፍ/ቤት ዘንድ ሊፈፀም የሚችል ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ በመረዳት ፍርዱ መቻቻል ሊደረግበት እንዲችል አፈፃፀሙ በአንድ ፍ/ቤት እንዲታይ በአሁኗ ተጠሪ በኩል የቀረበው የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበው የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲተላለፍ አድርጓል፡፡ የአሁኗ ተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻ ያቀረቡበት ፍርድ ገንዘቡን የአሁኗ አመልካችና ሌላው የፍርድ ባለዕዳ በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ ተብሎ የተወሰነ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ስለመቻቻሉም ጥያቄ አፈፃፀሙን በዝርዝር በማየት የሚወሰነው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች አንዱ በሌላው ላይ ያስወሰነው በፍርድ የበሰለ ገንዘብ በመቻቻል መፈፀም እንዲችል የአሁኗ ተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲተላለፍ ማድረጉ የሕግ ስህተት ያለበት አይደለም፡፡

የአሁኗ አመልካች የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1838 እና 1839ን በመጥቀስ ማቻቻል እንዲደረግ ባለዕዳው የሚፈልግ መሆኑ መረጋገጥ አለበት በሚል ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተም በፍርድ የበሰለው የገንዘብ ዕዳ መቻቻል አፈፃፀም የሚመራው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 397 መሠረት ስለሆነ ወደ ፍትሐብሄር ሕጉ ድንጋጌዎች የሚወሰድ ጉዳይ አይደለም፡፡ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 397/1/ የሚጠይቃቸው ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ ሆነው ከተገኙ ማቻቻሉ መፈፀም ይኖርበታል፡፡ በዚህ ጉዳይ መቻቻሉ እንዲፈፀም በሕጉ ላይ የተመለከቱት መሠረታዊ የሆኑት ነገሮች ተሟልተው ስለሚገኙ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር በሕጉ ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡

ሌላው አመልካች የአሁኗ ተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻ ባቀረቡበት ፍርድ ገንዘቡን እንድከፍል የተወሰነው በእኔ ላይ ብቻ ሣይሆን በዶ/ር አለኸኝ መኮንንም ላይ ስለሆነ እኔ በተጠሪዋ ላይ ካስፈረድኩት ገንዘብ ጋር መቻቻል ሊደረግበት አይችልም በሚል ያነሱትን የተቃውሞ ክርክርም በሚመለከት በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ ተብሎ የተወሰነ መሆኑን ተጠሪዋ በጽሑፍ በአቀረቡት መልስ ላይ የገለፁት ሲሆን አመልካችም በጽሑፍ በሰጡት የመልስ መልስ ላይ በአንድነትና በነጠላ ይከፈል መባሉን አልካዱም፡፡ በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ ተብሎ የተወሰነ ሆኖ ከተገኘ የፍርድ ባለመብቷ በሕጉ የአንደኛው የፍርድ ባለዕዳ ንብረት ብቻ ተሽጦ ወይም አፈፃፀሙ በአንደኛው የፍርድ ባለዕዳ ላይ ብቻ ቀጥሎ ገንዘቡ እንዲከፈላቸው መጠየቅ ይችላሉ፡፡ መቻቻሉም በተመሣሣይ መንገድ ተፈፃሚ የሚሆን ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች በተጠሪዋ ላይ ብቻ አስፈርደው የአፈፃፀም ማመልከቻ ያቀረቡበት ገንዘብ የአሁኗ ተጠሪ አመልካችና ሌላ ሁለተኛ ሰው በአንድነትና በነጠላ

ይክፈሉ ተብሎ ተወስኖ አፈፃፀም ከጠየቁበት ገንዘብ ጋር እንዲቻቻል ከተደረገ በኋላ አመልካች በሕጉ ያላቸው መፍትሄም ሆነ አማራጭ ሁለተኛው የፍርድ ባለዕዳ በድርሻቸው ያለውን ገንዘብ እንዲተኩላቸው መጠየቅ ስለሆነ ተጠሪ በእኔና በሌላ ሁለተኛ ሰው ላይ በፍርድ ያስወሰኑት ገንዘብ እኔ በተጠሪዋ ላይ ብቻ ካስወሰንኩት ገንዘብ ጋር መቻቻል እንዲፈፀም ሊደረግ አይገባም በሚል ያቀረቡት ተቃውሞ ተቀባይነት የለውም፡፡

አመልካች የአሁኗ ተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲያቀርቡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 386 መሠረት ለእኔም ማመልከቻው ተልኮልኝ ቀርቤ መልስ እንድንሰጥ መደረግ ሲገባው ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንን የመሰማት መብቴን አልፎ መቻቻል እንዲደረግ የተጠሪ የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይተላለፍ ያለው ያለአግባብ ነው ብለው የገለጹትን በተመለከተም አሁንም ቢሆን ፍርዱ እንዳይፈፀም የሚቃወሙበት የሕግ ምክንያት ስለመኖሩ ያስረዱት ነገር ስለሌለ በፍርድ ተወስኖ ባለቀ ጉዳይ ላይ እንደገና መልስ እንድሰጥ መደረግ ነበረበት የሚለው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ሁለት ፍርዶች በማቻቻል እንዲፈፀሙ በማድረጉ ሂደት ሊያነሱት የሚገባ ጥያቄ ካለ ማቅረብ የሚገባቸው የአፈፃፀሙን ጉዳይ በማየት ላይ ለሚገኘው ፍ/ቤት ነው፡፡

በአጠቃላይ ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች አንዱ በሌላው ላይ በፍርድ ያስወሰኑትን ገንዘብ የአፈፃፀም ጥያቄዎች በአንድ ፍርድ ቤት ታይተው በማቻቻል እንዲፈፀሙ የአሁኗ ተጠሪ ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቅርበውት የነበረው የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲተላለፍ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት የሌለ ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 56661 ሰኔ 14 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

/አተ